# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 184 ህዳር 14 2004 ገጽ 1


**የመምህር የኔሰው መስዕዋትነት ለሁላችንም የእግር እሳትና የልብ ህመም ነው። እሳቱ ይፍጀን!!! ህመሙ ይመመን!!! እናም የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝን "በቃህ!!!" የማለት ድፍረት ይኑረን።**

**በቃን!!! እኛም እንደየኔሰው ፍትህና ነፃነት በሌሉባት አገር ውስጥ መኖር አንፈልግም!!! መለስ ዜናዊንና ዘረኛ ቡድኑን ከሥልጣን አስወግደን የነፃነት አየር መተንፈስ እንሻለን፤ እናደርገዋለንም!!!**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የወያኔ አገዛዝ ሃሰተኛ ክስ የመሠረተባቸው የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ጋዘጤኞች ፍርድ ቤት ተብዬው የድራማ ችሎት ፊት ቀረቡ

ላለፉት 20 አመታት በአገራችንና በህዝባችን ላይ በፈጸመው ወንጀል ተረብሾ ህዝብ በማሸበር ላይ የሚገኘው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የአንድነት ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ በሆነው አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ በሽብርተኝነት ወንጀል የከሰሳቸው 24 የፖለቲካ ፓርቲ የአመራር አባላት፣ ጋዜጠኞች እና የፖለቲካ አክቲቪስቶች የክስ ቻርጅ በመለስ ዜናዊ ቀጭን ት ዕዛዝ በሚዘወረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ሦስተኛ ወንጀል ችሎት ፊት በትናንትናው ዕለት ረቡዕ ጠዋት ቀርቦ እንደተነበበ የዜና ምንጮቻችን ከስፍራው ከላኩልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።

እንደዜና ምንጫችን ዘገባ ረቡዕ ጠዋቱ 3፡40 ሰዓት ላይ በካቴና ታስረው ወደ ችሎት የቀረቡት በሀገር ውስጥ የሚገኙት ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 8 ያሉት ተከሳሾች ብቻ እንደሆኑና ሌሎቹ ከሀገር ውጪ ይኖራሉ የተባሉት በጋዜጣ ተጠርተው እንዳልቀረቡ ከሳሽ አቃቤ ህግ አስረድቶአል፡፡

በችሎቱ ላይ የቀረቡት ተከሳሾች በሙሉ ሰውነታቸው የመነሳቆልና የመክሳት ምልክት የታየባቸው ቢሆንም የፈጠራ ክስ ቻርጁ ሲነበብላቸው ሁሉም የፌዝ ፈገግታ በማሳየት በክሱ ላይ ተቃውሟቸውንና በፍርድ ሥርዓቱ ላይ እምነት የሌላቸው መሆናቸውን አሳይተዋል ተብለዋል።

በወያኔ ጌቶቻቸው የታዘዙትን ፍርድ ከመስጠታቸው በፊት በአገሪቱ ህግ ያለ ለማስመሰል ድራማ ማሳየትን ሙያ ያደርጉ የፍርድ ቤቱ ዳኞች የተከሳሾችን የግል ሁኔታ በጠየቁበት ወቅት አንደኛ ተከሳሽ የሆነው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበርና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አንዷለም አራጌ ሥራው የሙሉ ሰዓት ፖለቲከኛ ብሎ መመለሱን፣ 5ተኛው ተከሳሽ ክንፈሚካኤል ደበበ በረደድ (አበበ ቀሲቶ) ደግሞ በበኩሉ "ለሰው ልጆች ፍትህና ሠላም መስፈን የምንቀሳቀስ ሠላማዊ ታጋይ ነኝ" በማለት ራሱን ማስተዋወቁ ተዘግቦአል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በአርበኛው የኔሰው ገብሬ ላይ የተከፈተው የስም ማጥፋት ዘመቻ አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ምን ያህል የዘቀጠ እንደሆነ የሚያመላክት ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በህዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና በደል ልኩን አልፎ ከሚሸከመው አቅም በላይ እየሆነ በመምጣቱ ራሱን በቤንዚን አርከፍክፎ ህይወቱን የሰዋውን መምህር የኔሰው ገብሬን የህይወት መስዋዕትነት ለማድበስበስ ወያኔ ሆን ብሎ የፈጠረው "አይምሮው ጤናማ አልነበረም" የሚለው ሃሰተኛ ማስተባበያ አገዛዝ ያለበትን የወረደ የዝቅጠት ደረጃ በግልጽ የሚያመላክት ነው በማለት አስተያየት ሰጪዎች ተናገሩ። በዳውሮና አካባቢው የሚገኙና ስማቸው ፍጹም እንዳይገለጽ የጠየቁት ወጣቶች ለግንቦት ሰባት ዘጋቢ በስልክ እንደገለጹት፣ በአካባቢው ተወላጆች በተለይም በቅርበት በሚያውቁት ዘመድ ወዳጆቹና ጓደኞቹ ዘንድ አክብሮት የተቸረው የኔሰው ገብሬ ህይወቱን ለነጻነትና ለፍትህ ተቆርቋሪነት ከገበረ ቦኋላ ወያኔ በሚቆጣጠራቸው የተለያዩ የዜና ማሰራጫዎች አሳዛኝ የሆነ የስም ማጥፋት ዘመቻ የተከፈተበት መሆኑ እጂግ አስገራሚና አሳፋሪ ከመሆኑ አልፎ በርካታ የህብረተሰብ ክፍልን እንዳስቆጣ ገልጸው ይህ የወያኔ ድርጊት የበለጠ ለትግል እንደሚያነሳሳቸውና ጥያቄቸውም ምላሽ እስከሚያገኝ የየኔሰውን አርማ ይዘው አገዛዙን እንደሚታገሉት ገልጸዋል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እያካሄደ ያለው የስም ማጥፋት ዘመቻ ምናልባት የኔሰው ገብሬ ማን እንደሆነ በቅርበት የማያውቁትን ግር ሊያሰኝ ይችል ይሆናል ያሉ እኙህ ምንጭ ይሁን እንጂ እዚሁ አብረነው ተወልደን ላደግን፣ በቅርብ ለምናውቀው ተማሪዎቹና ጓደኞቹ ለሆነው የአገዛዙ ባለሥልጣኖች የፖለቲካ ጥቅም እስካገኙበት ድረስ ምን ያህል ሂሊናቸውን አውርደው ርካሽ የሆነ ፕሮፖጋንዳ መንዛት እንደሚችሉ እንድንታዘብ አድርጎናል ብለዋል። በመጨረሻም አስተያየት ሰጪዎቹ የኔሰው፣ በጣም አስተዋይ የነበረ፣ የሚያደርገውን ለይቶ የሚያውቅ የፍትህ መዛባት እጂግ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ኢትዮጵያ ሶማሊያን ዳግም መውረሯ ፍጹም ትክክል አይደለም ሲሉ በአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት የአፍሪካ ተጠሪ የሆኑት ጆኒ ካርሰን ተናገሩ

የኢትዮጵያ ጦር ወደሶማሊያ ግዛት ዘልቆ መግባቱን ተከትሎ በአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት የአፍሪካ ተጠሪ የሆኑት ጆኒ ካርሰን ኢትዮጵያ ሶማሊያን ዳግም መውረሯ ፍጹም ትክክል አይደለም ሲሉ ተናገሩ። ጆኒ ካርሰን ይህን የተናገሩት ማክላቺ ከተባለው ጋዜጣ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ነው።

ካርሰን ኢትዮጵያ ከአራት አመት በፊት ሶማሊያን በመውረር ለሁለት አመታት ያክል በአገሪቱ ውስጥ ብትቆይም፣ በመጨረሻ አልሸባብን ከመፍጠር በስተቀር ያመጣቸው ውጤት እንደሌለ ገልጸውና በሶማሊያ ሰላም ለማምጣት ማንኛውም እንቅስቃሴ በአፍሪካ ሰላም አስከባሪ በኩል መካሄድ እንዳለበት በመግለጥ የኢትዮጵያን እንቅስቃሴ በእጅጉ ነቅፈዋል።

የዘረኛውና አምባገነኑ መለስ አገዛዝ ቀደም ብሎ በተለይም የ1997 ምርጫን ተከትሎ በሃገሪቱ ተከስቶ የነበረውን ውጥረት አቅጣጫ ለማስቀየር በሶማሊያ ላይ ወረራ ፈጽሞ እንደነበር የሚታወስ ሲሆን ኢትዮጵያዊያን ወታደሮች ሶማሊያ ውስጥ ተገድለው አስከሬናቸው በመንገድ ላይ እስከሚጎተት መደረሱና የኢትዮጵያም ጦር ሶማሊያን ለቆ መወጣቱ አይዘነጋም።

የፋሽስቱ መለስ አገዛዝ በድጋሜ ሶማሊያን ለመውረር ለምን እንደፈለገ ግልጽ ባይሆንም፣ የፖለቲካ ተንታኞች የወያኔ አገዛዝ በምርጫ 97 ማግስት ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ መግባቱን ተከትሎ፣ የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስለወጥ ሲል ሶማሊያን መውረሩን በማስታወስ፣ አሁንም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዬው የህዝብ መከፋት እየጨመረ መምጣት ስጋት ላይ እየጣለው በመምጣቱ ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ መፈለጉን ያሳያል ይላሉ። እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት መንግስት ራሱን በጦርነት ውስጥ እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ በአገር ውስጥ የሚካሄደውን ተቃውሞ በጸረ ሽብር ትግል ስም ለመጨፍለቅ እንዲመቸው ለማድረግ የወሰደው እርምጃ ነው። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በአዲስ አበባ ከተማ የሚታየው የኑሮ ውድነት ከባድ ፈተና ሆኖብናል ሲል የወያኔ ሹም ኩማ ደመቅሳ አስታወቀ

ህወሃት ለሁለት በተከፈለበት ወቅት ከነ አቶ ተወልደ ቡድን ጋር በመወገኑ ከሥልጣን ተባሮ የነበረውና ቦኋላ ንሰሃ ገብቶ የመለስ ዜናዊን ቡድን በመቀላቀል ድህረ ምርጫ 97 የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ለመሾም የበቃው ኩማ ደመቅሳ በከተማው ውስጥ እየታየ ያለው የኑሮ ውድነት ከባድ ፈተና ሆኖብናል በማለት ከትናንት በስቲያ ማክሰኞ ለተሰበሰበው የወያኔ ፓርላማ አስታወቀ።

እንደ ኩማ ደመቅሳ አነጋገር ከተማውን ለከባድ ችግር ዳርጎታል የተባለው የኑሮ ውድነት መንስኤው አገዛዙ የዘረጋው ዘረኛ ድርጅታዊ መዋቅር እና የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሳይሆን በኢኮኖሚ የበለጸጉ አገሮች በገጠማቸው ቀውስ የተነሳ ነው። መለስ ዜናዊ ላለፉት 5 እና ከዚያም በላይ አመታት አገሪቷ በተከታታይ የሁለት አሃዝ እድገት አስመዝግባልች በማለት ባዶ ድስኩሮችን ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ በሚያሰማባቸው ወቅቶች አሁን የሚሳበብበት የአለም የኢኮኖሚ ቀውስ ምንም አንድምታ እንዳልነበረው ሲገለጽ የሰነበተ ቢሆንም ኩማ ደመቅሳና ሌሎች የበታች ባለሥልጣናት ግን የአለቃቸውን ቃል በመጻረር ችግሩን በሌሎች አገር ከተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ ጋር ለማመሳሰል ሲባዝኑ ይስተዋላል።

በማክሰኞ ዕለቱ የኩማ ንግግር ከተንጸባረቀው አንዱ "የአቅም ግንባታና የመልካም አስተዳደር እጦት ችግር እየተባባሰ መሄድ ሲሆን በአገር ሃብት ዘረፋና በሙስና የተዘፈቀው የወያኔ አገዛዝ በመንግሥታዊና አገልግሎት ሰጪ ተቋሞች ለፖለቲካ ሥር ዓቱ ታማኝነትንና ታዛዥነትን መስፈርት በማድረግ ምንም አቅምና ችሎታ የሌላቸውን ሰዎች ሲያሰማራ ቆይቶ አሁን ችግሩ የአገዛዙን የስልጣን ዕድመና ሂሊውና የሚፈታተንበት ወቅት ላይ ሲደርስ ማንን ለመወንጀል ወይም በማን ላይ ለማላከክ መወትወት እንደጀመረ የታወቀ ነገር የለም።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆኖ የተሾመውን ኩማ ደመቅሳን ጨምሮ የዛሬ 20 አመት ባዶ እጃቸውን አዲስ አበባ የገቡት አብዛኛዎቹ የወያኔ ባለሥልጣኖች ዛሬ ላካበቱት ሃብት መሠረቱ የአዲስ አበባን የከተማ መሬት በሚሪት እየወሰዱ አሳልፎ በመቸብቸብ የተገኘ እንደሆነ፤ የነርሱንም ዱካ ተከትለው ዛሬ በአቅም ማነስ እየተወነጀሉ ያሉት ካድሬዎች በሙሉ በዘረፋውና በሙስናው እንደተሰማሩ ህዝብ ጠንቅቆ ያውቃል።

## የኔሰው ገብሬ: ነፃነትን በእሳት የተቀዳጀ ሰማዕት!!!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በመምህር የኔሰው ገብሬ አስደንጋጭ መስዕዋትነት ምክንያት የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ይገልፃል። የመምህር የኔሰው ገብሬ መሰዋት ለቤተሰቦቹ፣ ለወዳጆቹና ለዳውሮ ዞን ነዋሪዎች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያዊያን ሁሉ መሪር ሃዘን ነው።

በደቡብ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግሥት በዳውሮ ዞን የሚገኘው የዋካ ከተማና አካባቢው ህዝብ በአስተዳደር በደል፣ በኑሮ ውድነትና በወረዳ አከላለል መነሻነት ከወር በላይ የዘለቀ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ ነው። የዞኑ ካድሬዎች "በእያንዳንዳችሁ በር ላይ ድንኳን ይተከላል፤ ሞት በአየር ላይ ይዘራባችኋል!" እያሉ ቢያስፈራሩም ህዝቡ ግን "የመብት ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ወደኋላ አንልም" ብሎዓል።

ዋካ በመለስ ዜናዊ ሠራዊት ተወራለች። የዋካ አዛውንቶችና ወጣቶች ታስረዋል፤ እየታሰሩም ነው። ተሰቃይተዋል፤ እየተሰቃዩም ነው። ሆኖም ግን ትግላቸውን ቀጥለዋል። ከእነዚህ ወጣት ታጋዮችና የበደል ሰለባዎች አንዱ ትውልዱ ጅማ የሆነው መምህር የኔሰው ገብሬ ነበር።

መምህር የኔሰው ገብሬ ከሥራ ተባሯል፤ ታስሯል፤ ተንገላቷል። ታስሮ ከብዙ ስቃይ በኋላ ሲፈታም ስለታሰረበትም ሆነ ስለተፈታበት ሁኔታ የሚነግረው አላገኘም። የሰው ልጅ በዘፈቀደ እየታሰረ የሚሰቃይበት ሥርዓት ተወግዶ፤ ፍትህ የሰፈነባትን ኢትዮጵያ ለማየት ጓጉቷል።

ኅዳር 1 ቀን 2004 ዓ.ም. መምህር የኔሰው፣ በእርሱ ላይ እንደደረሰው ሁሉ ያለአግባብ የታሰሩ ወዳጆቹ ወደ ሚቀርቡበት የወረዳው ፍርድ ቤት አመራ። ወዳጆቹ ይፈታሉ ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር። ሆኖም ዳኛው የታዘዙትን ተጨማሪ ቀጠሮ የመስጠት ውሳኔ አስተላለፉ። የየኔሰው ትዕግሥት ገደቡ አለፈ። ከፍርድ ቤቱ እንደወጣ ወደ አካባቢው አስተዳደር ቢሮ ሄደ። ባለስልጣኖቹ ስብሰባ ላይ ናቸው። የአስተደደሩ ቢሮ በረንዳ ላይ *"በደል በዛ!!! ፍትህ በሌለበት አገር መኖር አልችም!!! በዚህ ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም!!! ግፍና መከራ እያየሁ መኖር አልችልም!!!"* እያለ ቤንዚን በራሱ ላይ አርከፍክፎ እሳት ለኮሰ።

መምህር የኔሰው በቂ የህክምና እርዳታ ቀርቶ ጠያቂ እንኳን በወጉ አጠገቡ እንዳይደርስ በፓሊስ እንደተከለከለ ኅዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም. በተርጫ ሆስፒታል ውስጥ ህይወቱ አለፈች።

*ኅዳር 4 ቀን 2004 ዓ.ም. ኢትዮጵያም አንድ በፍትህ እጦት የተከፋና የተቆጣ ልጇን አጣች።*

በመምህር የኔሰው ቀብር ላይ መገኘት የሚያሳስር ወንጀል መሆኑ በመለስ ዜናዊ ካድሬዎች ቢነገርም፣ በርካታ ህዝብ የመጨረሻውን አሸኛኘነት አደረገለት። ኅዳር 5 ቀን የመምህር የኔሰው ገብሬ አስከሬን መቃብር ውስጥ አርፎ "ግብዓተ-መሬት" ቢፈፀምም፣ ታሪኩ ግን ከመቃብር በላይ ውሎ በመላው ዓለም እየናኘ ነው።

የመምህር የኔሰው አሟሟት የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ አስከፊነት መገለጫ ሆኗል። መምህር የኔሰው የፍትህ ዋጋ ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ማሳያ ሆኗል። መምህር የኔሰው በህይወት እያለም፤ እየሞተም፤ ከሞተም በኋላ መምህር ሆኖ አስተምሮናል። መምህር የኔሰው፣ "እየኖርን ነን" እያልን እራሳችንን እያታለልን ላለነው ሁሉ ከፍ ያለ የሞራል እዳ ጥሎብን አልፏል።

በ1997 ምርጫ ማግሥት ባለቤታቸውን ከአጋዚ ወታደሮች ለማስጣል በመሞከራቸው በመትረየስ እሩምታ የተገደሉት የወ/ሮ እቴነሽ ይማም ልጅ "እናቴን ቅንጅት ነው የገደላት ብለሽ መስክሪ" ተብላ እንደነበር ሁላችንም እናስታውሳለን። እንዲሁም የትምህርት ቤት ዩኒፎርማቸውን እንደለበሱ፤ የደብተርና እስክርቢቶ ቦርሳዎቻቸውን እንዳነገቡ፣ የተደፉት እነ ህፃን ነቢዩ ሳይቀሩ "ባንክ ሊዘርፉ ሲሉ ነው የተገደሉት" መባሉ መቼም ቢሆን የሚረሳ አይደለም።

ዛሬም የመለስ ዜናዊ የውሸት ፋብሪካዎች መምህር የኔሰው ገብሬ የአዕምሮ ህመምተኛ ነበር እያሉ ማስወራት ጀምረዋል። የዋካ ነዋሪዎች ግን በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ "ለፍትህ መቆም እብድ ያሰኛል?" እያሉ እየሞገቷቸው ነው። በአንፃሩም መምህር የኔሰው የእውቀት ጥማት የነበረው፤ ከፍተኛ የማንበብ ፍቅር የነበረው ወጣት እንደነበር ወዳጆቹ ሁሉ ይመሰክራሉ።

ለመሆኑ የመምህር የኔሰው መስዋዕትነት ለትግላችን ያለው አንደምታ ምንድነው? መምህር የኔሰው በመስዋዕትነቱ ያስተላለፈው መልዕክት ምንድነው?

የመምህር የኔሰው መልዕክት ግልጽ ነው። ፍትህና ነፃነት በሌሉበት፤ መብት በተረገጠበት ሁኔታ መኖር ኑሮ አይባልም። የባርነት ኑሮ፤ ኑሮ አይደለም። እውነቱን ለመናገር ባለፉት ሃያ ዓመታት ኢትዮጵያዊያን እየኖርን ያለነው "ኑሮ" ኑሮ አይደለም። ዓይኖቻችን እያዩ፤ ጆሮዎቻችን እየሰሙ አንድ ጠባብ፣ ዘረኛና ትዕቢተኛ የሆነ ትንሽ ቡድን፣ መላዋን ኢትዮጵያ ጠፍንጎ አስሮ እያለባትም፤ እያዋረዳትም ነው። አገራችን በአንድ ቡድን ስትመዘበር መከላከል አቅቶን በድናችንን እየኖርን ነው። ባርነት ይለመዳል። እኛም ለሃያ ዓመታት ባርነትን ተለማምደናል። መምህር የኔሰው የለኮሳት እሳት ካላነቃችን መቼም ላንነቃ እንችላለን።

የመምህር የኔሰው መስዕዋትነት ለሁላችንም የእግር እሳትና የልብ ህመም ነው። እሳቱ ይፍጀን!!! ህመሙ ይመመን!!! እናም የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝን "በቃህ!!!" የማለት ድፍረት ይኑረን።

በቃን!!! እኛም እንደየኔሰው ፍትህና ነፃነት በሌሉባት አገር ውስጥ መኖር አንፈልግም!!! መለስ ዜናዊንና ዘረኛ ቡድኑን ከሥልጣን አስወግደን የነፃነት አየር መተንፈስ እንሻለን፤ እናደርገዋለንም!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

.....................................................................................................

## የመምህር የኔሰው አሙዋሙዋት የበርካታ ዜና አውታሮች ሽፋን ሆኖ ሰነበተ ዓለም አቀፍ ትኩረትንም እየሳበ ነው

የአረመኔውን የወያኔ አገዛዝ ግፍና በደል በመቃወም ራሱን በቤንዚን አርከፍክፎ በማቃጠሉ ኢትዮጵያዊው ቡአዚ የሚል ቅጽል ስም እየተሰጠው ያለው አርበኛው መምህር የኔሰው ገብሬ በተለይም በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ ባሉት ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ ሲሰነብት በርካታ የሬዲዮ ፕሮግራሞችና የመረጃ ድረገጾች ሰፊ ሽፋን ሰጥተው ሲዘክሩት ሰንብተዋል።

በሃገር ውስጥ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ በርካታ ወጣቶች የመምህር የኔሰው ገብሬ ሞት ከመቼውም በላይ የዘረኛውን አገዛዝ ለመጣል ለሚደረገው ትግል የሚያነሳሳቸውና ጽናትንም የሚሰጣቸው መሆኑን መግለጻቸውን አዲስ አበባ የሚገኘው ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ዘገባ አመልክቱአል። ወጣቶቹ ለዘጋቢያችን እንደተናገሩት የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ግፍና በደል ሞልቶ የተረፈው ለየኔሰው ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያዊያን ጭምር በመሆኑ፣ የየኔሰው ሞት መከፈል የሚገባውን መስዋእትነት በመከፈል አምባገነኑን አገዛዝ በሚቻለው መንገድ ሁሉ ለመጣል በቆራጥነት እንዲነሱ እንደሚያነሳሳቸውና አደራም እንደሆነባቸው ገልጸዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመላው አለም የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን፣ በቅርቡ ዘረኛና አምባገነኑን የወያኔን አገዛዝ በመቃወም ራሱን መስዋእት ያደረገውን መምህር የኔሰው ገብሬን ከፍተኛ የመወያያ አጀንዳቸው አድርገው የሰነበቱ ሲሆን ኢትዮጵያዊያኑ የኔሰው ገብሬ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና መከራ የመጨረሻው ደረጃ ላይ መድረሱን ማረጋገጫ ነው፣ እናም ሊከፈል የሚገባው መስዋ እትነት ሁሉ ተከፍሎ አገዛዙ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲወገድ የማድረጊያችን ወቅት አሁን ነው ብለዋል።

የየኔሰው ገብሬ መስዋእትነት የዘረኛውን አገዛዝ በሚቃወሙ የኢትዮጵያዊያን የመረጃ ድረገጾች፣ ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶት የሰነበተ ሲሆን የአለም አቀፍ የዜና አውታር የሆነውን ቢቢሲን፣ እንዲሁም ቪ ኦ ኤና የጀርመን ሬዲዮ ጣቢያዎች ሽፋን ሰጥተውታል።

በሌላም በኩል የፌስ ቡክ ተጠቃሚ ኢትዮጵያውያኑ ቀደም ብሎ በየፌስ ቡክ አድራሻቸው ላይ ይጠቀሙባቸው የነበሩ የየራሳቸውን ፎቶግራፎች በማንሳት በምትኩ የኔሰው ገብሬን ፎቶግራፍ የሚጠቀሙበትን ምክንያት አንዳንዶች እንደገለጹት "ወንድማችን የኔሰው በሀገራችን ውስጥ ነጻነት፣ ዲሞክራሲ እና የህግ የበላይነት እንዲመጣ ካለው ከፍተኛ ፍላጎት በመነሳት እራሱን በእሳት አቃጥሎ መሰዋቱን በቀላል እንደማንመለከተው እና እሱ የተሰዋለትን አላማ አንግበን እንደምንታገል ለመግለጽ ነው" ብለዋል። ሌሎች ደግሞ ሲያስረዱ "ጉዳዩ አገር አቀፍና አለም አቀፍ ትኩረት እንዲያገኝ"መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የዬኔሰው ገብሬ አድናቂ ኢትዮጵያዊያን የሀዘን መግለጫዎችንና የተነሱ ጥሪዎችን እያስተላለፉ ሲሆን የቶሮንቶ የሰብአዊ መብቶችና የዲሞክራሲ ህብረት በየኔሰው ገብሬ ሞት የተሰማውን ሀዘን ገልጦ፣ የካናዳ መንግስት ለመለስ ዜናዊ መንግስት የሚሰጠውን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያቋርጥ ጠይቋል። የኢትዮጵያ ወጣቶች ለለውጥ አባል የሆነው ዮናታን ወግደረስ በበኩሉ የየኔሰው ሞት ለሁለት ቀን ያክል ህመም ፈጥሮበት እንደነበር ገልጦ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የግፍ አገዛዝ እንዲያበቃ ሁላችንም በጋራ እንነሳ ሲል ጥሪ አቅርቧል።

ታዋቂው የህግ ባለሙያና ጸሀፊ የሆኑት ፕሮፌሰር አለማዬሁ ገብረማርያም ደግሞ "ነጻነቴን ስጡኝ ወይም ግደሉኝ" በሚል ርእስ ባወጡት ጽሁፍ የኔሰው ፣ በአለም ላይ ለነጻነታቸው ሲሉ ራሳቸውን ከሰውትና ለዘላለሙ በታሪክ ሲዘከሩ ከሚኖሩ ጀግኖች መካከል ተቀላቅሎአል" ብለዋል።

## በአርበኛው የኔሰው ገብሬ ላይ የተከፈተው የስም ማጥፋት ዘመቻ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

የሚያበሳጨውና፣ ይህንንም በግልጽና ባደባባይ የሚጋፈጥ ሰው ነበር፤ የኮሌጅ ተማሪ በነበረበት ጊዜ በጣም ጎበዝና የኮሌጁ ተሸላሚ የሆነ፣ አዘውትሮ መጻህፍት የሚያነብና አዋቂም ሰው ነበር ካሉ በሁላ፣ ጭራሹኑ የየኔሰው እህት ወንድሜ እብድ ነበር አለች ተብሎ በዜና መገለጹ ለመግለጽ የሚከብድ አሳፋሪና የዘቀጠ ድርጊት ነው ብለዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ ዶቼቬለ የአማርኛ ዜና አገልግሎት በስዊድን ሃገር ነዋሪ የሆኑትን አቶ ፍስሃ ተሰማ የተባሉ የዋካ አካባቢ ተወላጅን ያነጋገረ ሲሆን አቶ ፍስሃ መምህር የኔሰው ገብሬን፣ እህቱንና ቤተሰቦችንም በሚገባ እንደሚያውቁ ገልጸው፣ የመምህሩ መሞት ብቻ ሳይሆን በተለይም ከሞተ በኋላ የሚነዛው የፈጠራ ወሬ ይበልጥ እንዳሳዘናቸው፣ የኔሰው ከሞተ በኋላ ለፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ የሚነዛው ወሬና ማብራሪያ እንደሆነ ገልጸዋል። አቶ ፍስሃ ቀጥለውም ከመሞቱ በፊት ህዝብን ቀስቅሰሃል፣ የወረዳውን ችግር ጥያቄ አቅርበሃል፣ በሚል ነበር ታስሮ የነበረው። ይህ ታስሮ የነበረ ሰው (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሰቆቃን ለማስቆም በጋራ እንነሳ!!!

### የግንቦት 7 ድምጽ በርዕሰ አንቀጽ ቁጥር 134 አውጥቶት የነበረና ከወቅታዊነቱ የተነሳ ዳግም ለህትመት የበቃ

ከወያኔ እስር ቤቶች የሚደርሱን መረጃዎች ህሊናን የሚረብሹ ናቸው። የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ አባላት በእስር ላይ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ የሚፈጽሙት ሰቆቃ (ቶርቸር) በአስከፊ ሁኔታ ጨምሯል።

በጭካኔው "ተወዳዳሪ የለውም" ሲባል በነበረው የደርግ ዘመን እንኳን የማይታወቁ የሰቆቃ ዓይነቶች ዛሬ በንፁሃን ዜጎች ላይ እየተፈጸሙ ነው። ለማስረጃ ያህል:-

- ወንዶች የዘር ፍሬዎቻቸውን በመዶሻ ይቀጠቀጣሉ፣
- ሴቶች ጡቶቻቸውን ይረገጣሉ፤ ክብረ-ነክ ተግባራትም ይፈጸምባቸዋል፣
- በኤሌክትሪክ በሚሰራ ማሞቂያ የእስረኞችን ጭንቅላት በማጋል እንዲሰቃዩ ይደረጋል፣
- ከወንበር ጋር አቆራኝቶ ለሳምንት ያህል ማሰር በጣም እየተዘወተረ ያለ የሰቆቃ ዓይነት ሆኗል፣
- በጠባብ ክፍል ውስጥ ለብቻ ዘግቶ ለወራት ማቆየት የተለመደ ነገር ነው፣
- ከቆዳ በተሰራ ጅራፍ መግረፍ ድሮም ያለ ቢሆንም አሁን ተጠናክሮ ቀጥሏል፤
- በደርግ ጊዜ የነበሩ ገራፊዎች ከያሉበት እየተፈለጉ እንደገና ለገረፋ ተቀጥረዋል፣
- በሰብዓዊ ፍጡር ላይ ካራቴና ጁዶ መለማመድ፤ በስለት መቆራረጥ ወጣት የወያኔ "ተተኪዎች" የሚወዱት መዝናኛ ሆኗል፣

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ አሰቃቂ የሰቆቃ ዓይነቶች የወያኔ እስር ቤቶች መለያ ባህሪያት ናቸው።

የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ ሰላዮች ሰቆቃን የሚፈጽሙ ስለመሆኑ በገሃድ አምነው አያውቁም። ሆኖም ግን ሰቆቃን የሚፈጽሙት ተከልለውና ተደብቀው አይደለም። ስንቱ ነው ከተማ ውስጥ በሰው መሃል የተደበደበው? ስንቱ ነው በአደባባይ የተረገጠውና የተዋረደው? በጠራራ ፀሃይ፤ ከተማ ውስጥ፤ ህዝብ መሃል ይህንን የመሰለ ሰቆቃ የፈጸመን እስር ቤት ውስጥ ከዚህ አንድ ሺህ ጊዜ የከፋ ነገር ከመፈጸም ምን ያግደዋል?

በማናቸውም ምክንያት ሰቆቃ መፈጸም እጅግ የተወገዘ እና ምህረት የማያሰጥ ዓለም ዓቀፍ ወንጀል ነው። የደህንነት ስጋትም ሆነ አደጋ ለሰቆቃ በምክንያትነት ሊቀርብ አይችልም። ሰቆቃን ተቀባይነት ያለው የምርመራ ዘዴ የሚያደርግ የወንጀል ዓይነት የለም። "ወንጀል መከላከል" ለሰቆቃ ተቀባይነት የሌለው ምክንያታቸው ቢሆንም እንኳን ወያኔዎች እሱንም በምክንያትነት ማቅረብ አይችሉም። የወያኔ ሰላዮችና ፓሊሶች ሰቆቃን የሚፈጽሙት የሚመረምሩት ብርቱ ወንጀል ስላለ አይደለም። ወያኔዎች በወያኔ ዳኞች ጉዳያቸው ያለቀላቸውና ወያኔያዊ ፍርደገምድል ፍርድ የተሰጣቸው ፍርደኞችንም ጭምር ያሰቃያሉ። ለወያኔ የሰቆቃ እውነተኛ ምክንያቶች ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያዉና እና ዋነኛው ምክንያታቸው የዘር ጥላቻ ነው። የወያኔ አረመኔዎች የአማራና የኦሮሞ ተወላጆች የሆኑ ግለሰቦችን በደበደቡና ባዋረዱ መጠን አማራንና ኦሮሞን ያዋረዱ ይመስላቸዋል። ለዘመናት በልባቸው ውስጥ የተጠራቀመውን ጥላቻ በግለሰቦች ላይ ይወጡታል። እነዚህ በክፋት የተሞሉ ሰዎች ሲገርፉና ሲደበድቡ የሚሳደቡት፣ የሚራገሙት የተደብዳቢውን ዘር እንጂ ተደብዳቢውን በግል አለመሆኑ የደረሰበት ሁሉ ያውቀዋል።

ሁለተኛው ምክንያት የጉጅሌው አባላትና ተባባሪዎች ሰውን በማሰቃየት የሚደሰቱ እኩያን መሆናቸው ነው። ይህ የስነልቡና ህመም ምንጩ በራስ የመተማመን እጦት ነው። መንፈሰ ደካማ ሰው ውስጡ እየነገረው ያለውን ደካማነት በእጆቹ በሚሰነዝረው ዱላ ማስተባበል ይፈልጋል። የትግራይ ገዢ ጉጅሌ እና ተባባሪዎቹ የሚያደርጉት ይህንኑ ነው። እጃቸው ውስጥ የገቡትን ወገኖቻችንን በማሰቃየት ትንሽነታቸውን ማሸነፍ ይፈልጋሉ።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በወገኖቻችን ላይ ዘግናኝ ሰቆቃዎችን በማድረስ ላይ ለምትገኙ የትግራይ ገዥ ጉጅሌ አባላት፣ ለቅጥረኞቻቸውና ተባባሪዎቻቸው በሙሉ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል። ሰቆቃ ፈጽሞ ማምለጥ እንደማይቻል በደርግ ጊዜ የሰቆቃ ቀንደኛ መሪ ከነበረውና በአሜሪካ አገር ተከሶ ዛሬ በናንተው እስር ቤት ከሚገኘው ቀልቤሳ ነጌዎ ትምህርት ውሰዱ። የእናንተም መጨረሻ ከእነሱ የባሰ እንጂ የተሻለ እንደማይሆን ተገንዘቡ።

ግንቦት 7 በሰቆቃ ላይ መረጃ ማሰባሰብ የጀመረ በመሆኑ ያላችሁን መረጃዎች
በኢሜል pr@ginbot7.org እና
በፓስታ P.O.Box: 56281, London N4 9BH, United Kingdom
P.O.Box: 4916, 2003EX, Haarlem, The Netherlands
8647 Richmond Highway, 652, Alexandria, VA 22309, USA

እንትልኩ ያሳስባል።

## የኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች ሃገራቸውን ጥሎ መሰደድ ቀጥሎአል፣ የሲ.ፒ.ጄ የ2010- ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት ሽልማት አሸናፊ የሆነው የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ አገሩን ጥሎ ተሰደደ

የዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ የሚያደርስባቸውን ግልጽና ስውር አፈና ተቋቁመው ህትመት ላይ ቀርተው ከነበሩ ጋዜጦች መካከል የአውራ አምባ ታየምስ ጋዜጣ ዋና መስራችና አዘጋጅ የነበረው ዳዊት ከበደ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጋዜጠኞች ላይ የተከፈተው አዲስ ዙር መንግሥታዊ ሽብርና ዛቻ ለህይወቱ አስግቶት አገር ጥሎ መኮብለሉን ኢሳት በትናትናው የዜና እወጃ ፕሮግራሙ ዘግቦአል።

የጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ አገር ጥሎ መሰደድ ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ለስደት የተዳረጉ ጋዜጠኞችን ቁጥር ሶስት ያደረሰው ሲሆን ጋዜጠኛ ዳዊት ሲ.ፒ.ጄ የተባለው አለም አቀፍ የጋዜጠኞች መብት አስከባሪ ድርጅት የ2010- ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት ሽልማት አሸናፊ ያደረገው ወጣት ጋዜጠኛ እንደሆነ ይታወቃል።

የ1997 ምርጫን ተከትሎ ከቅንጅት መሪዎችና ከሌሎች ጋዜጠኞች ጋር ታስሮ የነበረውና ዕድሜ ልክ ከተፈረደበት በሁዋላ በይቅርታ የተፈታው ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ፣ የሚወዳትን አገሩን ጥሎ ለመሰደድ የተገደደበትን ምክንያት ሲገልጽ፤ የፖለቲካ ተቀናቃኞችንና ነጻ ጋዜጠኞችን ሆን ብሎ በማጥቃት ዳግም የምርጫ 97 አይነት ህዝባዊ የለውጥ መነሳሳት በአገሪቱ እንዳይፈጠር ሲባል ተረቆ ሥራ ላይ በዋለው የጸረ ሽብርተኝነት ህግ አዋጅ ሊከሰስ የፈጠራ ወንጀሎች እየተቀነባበሩበት መሆኑን ማስረጃ ስለደረሰው መሆኑን ገልጾአል።

የጸረ ሽብርተኝነት ህግ አገርንና ዜጎችን ከአሸባሪዎች ለመከላከል ተግባር መዋል ሲኖርበት መለስ ዜናዊ ግን የፖለቲካ ተቀናቃኞችንና ነጻ ሂሊና ያላቸውን ዜጎች ለማጥቃት እያዋለው ነው ያለው ጋዜጠኛ ዳዊት፤ በየትኛውም የአለማችን ክፍል ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ የሽብርተኝነት ትርጉም አገራችን ውስጥ ተፈጥሮ በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ እንደመድረክ አይነቶቹ ድርጅቶች ሁሉ በሽብርተኝነት እየተወነጀሉ ነው ብሎአል።

በርሱና በሙያ ባልደረቦቹ ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃትና ስጋትም ሲገልጽ እነ ውብሸት ታዬ፣ እስክንድ ነጋና ርእዮት አለሙ በሽብረተኝነት ተከሰው ማዕከላዊ እስር ቤት ከተወረወሩ ጊዜ ጀምሮ ስራቸውን በከፍተኛ ስጋትና ጭንቀት ውስጥ ሆነው ለማከናወን እንደተገደዱ አልሸሸገም።

አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን እየደረሰባቸው ያለውን ግፍና በደል የሚያጋልጡና በአገዛዙም ላይ የሰላ ሂስ በሚያቀርቡ ጋዜጠኞች ሃገራቸውን ጥለው እንዲኮበልሉ የሚያደርግ ዛቻና ማስፈራሪያ እየፈጸመ መሆኑ በተከታታይ የተዘገበ ሲሆን በቅርቡ የፍትህ አምደኛ የሆነው ታዋቂው ሀያሲ አቤ ቶክቾው ወይም አበበ ቶላ፣ ከደህንነት ሀይሎች የተሰነዘረበትን ማስፈራሪያ ተከትሎ ከአገር መውጣቱ መዘገቡ ይታወሳል።

በሌላም በኩል የወያኔው አገዛዝ ጠንካራ ሂስ የሚያቀርቡበትን ጋዜጠኞች አሸባሪ እያለ ወደ እስር ቤት ማጎሩን በማስመልከት አለማቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅት ማውገዙ ይታወሳል።

## ኢትዮጵያ ሶማሊያን ዳግም መውረሯ ፍጹም ትክክል አይደለም . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በሌላ በኩል ደግሞ የአካባቢው አገሮች በተለይም ዩጋንዳና ኬንያ በሶማሊያ ውስጥ ያላቸው ጉልበት እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ፣ የፋሽስቱ መለስ አገዛዝ ከምእራቡ አለም የሚያገኘው የዲፕሎማሲና የገንዘብ ድጋፍ እንዳይቋረጥ በመስጋት የወሰደው እርምጃ ነው የሚሉ አሉ።

እንደ ማከላቹ ጋዜጣ ከሆነ ሶማሊያውያን የኢትዮጵያ ጦር ወደ አገራቸው መግባቱን አይደግፉም። የአልሸባብን አስተዳደር በርካታ ሶማሊያውያን እንደሚጠሉት ያስታወሰው ጋዜጣው፣ አንዳንዶች የኢትዮጵያ ጦር ሶማሊያ ከሚገባ አልሸባብ ይግዛን እስከማለት መድረሳቸውን ገልጿል።

የኢትዮጵያ ጦር ወደ ሶማሊያ መግባቱ እውነት መሆኑ በስፋት እየተዘገበ ባለበት ባሁኑ ሰአት፣ የፋሽስቱ አገዛዝ እንደተለመደው አይኔን ግምባር ያድርገው በማለት አሁንም ጦሩ ወደ ሶማሊያ መግባቱን ያስተባብላል።

## ወያኔ የመረጃ ፍሰትን ለመቆጣጠር በኢንተርነትና ስልክ አገልግሎት ላይ የጣለው ቁጥጥር ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሚገኙ የውጪ አገር ኤምባሲዎችን ጭምር እንዳስመረረ ተዘገበ

በአገራችን የተዘረጋው የስልክና የኢንተርኔት አቅርቦት ወያኔ ሃሳብን በነጻነት የማለጽ መብት ለመገደብና ዜጎች ስለአገራቸውና ስለሚያስተዳድራቸው መንግሥት በቂ መረጃ እንዳያገኙ ለመከላከል እንዲያስችል ተደርጎ የተዋቀረ በመሆኑ፤ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ የሆኑ ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆነ አለም አቀፍ ድርጅቶችና ዲፕሎማቲክ ሚሽኖች ጭምር እያስመረረ መምጣቱን ባለፈው ሳምንት ይፋ የሆነ ዜና አረጋገጠ።

በወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ሥር የሆነው የኢትዮ ቴሌኮም ኮርፖሬሽን ከደንበኞቹ ጋር ባለፈው ሳምንት በሂልቴን ሆቴል ባካሄደው የሃሳብ ልውውጥ ላይ የተሳተፉ የበርካታ አገራት ኢምባሲ ተወካዮች እንደገለጹት፤ የተለያዩ አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች ጽቤት በሚገኝበት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ እየታየ ያለው የስልክና የኢንተርኔት አገልግሎት አቅርቦት እጅግ የሚያስመርር ኋላቀርና ደካማ መሆኑን ገልጸው ይህ አሰራር ባፋጣን ሊሻሻል ግድ ይላል ብለዋል።

ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ ከሆኑ ኤምባሲዎችና አለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካይ በተጨማሪ በውይይቱ ላይ ከተሳተፉ አገራዊ መሥሪያቤቶች መካከልም አንዳንዶቹ በአቅርቦቱ ኋላቀርነት መማረራቸውን እንደገለጹ የተዘገበ ሲሆን የአዲስ አበባ መስተዳድር ጽህፈት ቤትም ከቅሬታ አቅራቢዎቹ አንዱ እንደነበር ተዘግቦአል።

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ የአፍሪካ መዲና የሆነችው ኢትዮጵያ በስልክና በኢንተርኔት አገልግሎት፤ ከመንግስት አልባዋ ሶማሊያ ሳይቀር የማትሻልና ከአፍሪካ አህጉር መጨረሻ ላይ የምትገኝ ናት።

የኢንቴርኔት አገልግሎት በቱኒዚያና ግብጽ ሚሊዮኖችን ለለውጥ በማነሳሳት አገልግሎት ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ወያኔ በወሰደው ጠበቅ ያለ የአፈና እርምጃ ወትሮውኑ የአገልግሎት አቅሙ ደካማ የነበረው የአገራችን የኢንተርኔት አቅርቦት ከነበረው አቅም በታች እንዲወርድ በመደረጉ በርካታ ድርጅቶችና ተቋሞች አገልግሎቱን ማማርር አዘወትረዋል።

ቀደም ሲል የ ኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒከሽን ባለሥልጣን በመባል ይታወቅ የነበረው መንግሥታዊ ተቋም ውስጥ የሚሰሩ የስራ ሃላፊዎችና በርካታ ሺ ሠራተኞች ተባረው በቻይና በሰለጠኑ የህወሃት አባላትና ከመከላኪያ ሰራዊት በተገለሉ ሰዎች እንዲያዝ መደረጉ ሲዘገብ ቆይቶአል።

ባለፈው ሳምንት የወያኔን ኢፍትሃዊነት በመቃወም ራሱን በ እሳት አቃጥሎ የሰዋ የመምህር የኔሰው ገብሬ ዜና እንደተሰማ፤ ወደ አካባቢው የሚደረጉ የስልክ ጥሪዎች በአስቸኳይ ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ መደረጋቸው አይዘነጋም። የኢትዮ ቴሌኮም ወያኔ የዘጎችን ስልክ መስመር ለመጥለፍ የሚያደርገውን ሥራ እያገዘ መሆኑ በቅርቡ በቅርቡ በአቶ ኤልያስ ክፍሌ መዝገብ ተከሰው ፍርድ ቤት በቀረቡት በአቶ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬና መምህርት ርእዮት አለሙ ላይ የቀረበው የስልክ ንግግር መረጃ አጋልጦአል።

## የወያኔ አገዛዝ ሃሰተኛ ክስ የመሠረተባቸው የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ጋዘጤኞች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ወያኔ የሱዳን ጸጥታ ሰራተኞችን በገንዘብ ሃይል ገዝቶ ከተሰደደበትና በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ሥር በስደተኝነት ተመዝግቦ ከሚኖርበት ሱዳን አገር በጉልበት ተይዞ መጥቶ እስር ላይ የሚገኘው 8ተኛ ተከሳሽ የሆነው አንዷለም አያሌው ገላው ደግሞ "ለጊዜው ሥራ የለኝም፤ ከምኖርበት ካርቱም የስደተኛ ጣቢያ ነው ተይዤ የመጣሁት፤ ስለዚህ አድራሻ የለኝም፣ ቀደም ሲል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላ ሳለሁ የተሰጠኝን ቤት ባለቤቴንና ሁለት ልጆቼን አስወጥተው በአሁኑ ሰዓት የት እንዳሉ እንኳ አላውቅም" በማለት መመለሱን ለማወቅ ተችሎአል።

አቃቤ ሕግ ተብዬው የወያኔ ቃል አቀባይ ቀደም ብሎ ባቀረበው የክስ ቻርጅ ላይ እርማት አለኝ በማለት ፍርድ ቤቱን በመጠየቁ በተሰጠው እድል በ24ቱም ተከሳሾች ላይ አቅርቦት የነበረውን 1ኛ ክሥ፣ ከ1ኛ ተከሳሽ እስከ 22ተኛ ተራ ቁጥር ባሉት ተከሳሽ ላይ ብቻ ይጽናልኝ በተራቁጥር 23ና 24 የተጠቀሱት ከክሱ ውጪ ይሆኑልኝ በማለቱ የቀድሞው አዲስ ነገር ጋዜጣ ዋና አዘጋጅና ማኔጂንግ ኤዲተር መስፍን ነጋሽና ዐብይ ተክለማርያም ከአንደኛው ክስ ውጪ እንዲሆኑ ተደርገአል፡፡

ዐቃቤ ህግ ባቀረበው የክስ ቻርጅ ላይ በሁለተኛው ክሥ ከተከሳሽ ተራ ቁጥር 1 እስከ 18 ድረስ የሚለውን በ21ኛ እና በ22ተኛ ተራ ቁጥር ተከሳሾችም ላይ እንዲካተት ያደረገ ሲሆን፣ በ2ተኛው ክሥ 2ተኛ መስመር ላይ ከ2 እስከ 6ተኛ ተራ ቁጥር የሚለው ላይ 7ተኛ ተራ ቁጥርም በክሱ ላይ እንዲካተት አድርጓል፡፡

የተከላካይ ጠበቆች በበኩላቸው በክሱ አቀራረብ ላይ ተቃውሚቸውን ያቀረቡ ሲሆን፣ በተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ፣ በሽብርተኝነት፣ በሀገር መክዳትና የስለላ ተግባር ሲሆን፣ ይህም ከእድሜ ልክ እስከ ሞት ፍርድ ድረስ የሚያስቀጣ ቢሆንም ዐቃቤ ህግ ባቀረባቸው የክስ ቻርጅ ላይ ይህን የሚያመለክት የህግ መርሆዎችን የማያሟላ ተራ አሉባልታ እና ተከሳሾቹ በህገ መንግሥቱ መሠረት በህግ ተቋቋሞ በሰላማዊ መንገድ የሚታገል የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር አባላት እና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በመጠቀም የሚሰራ የጋዜጠኝነትና የፖለቲካ ትንታኔ ሥራዎች የሚያከናውን ጋዜጠኛ እስከንድር ነጋ በህጋዊ ሥራዎቻቸውና በግል መብታቸው ነው የተከሰሱት በማለት አብራርተዋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት ተብየው የወያኔ ካድሬዎች ስብስብ አሸባሪ ብሎ በቅርቡ ከወሰነው የግንቦት 7 አመራር አባላት ጋር አንድ ላይ መከሰሳቸው ዐቃቤ ህግ ሆን ብሎ በተከሳሾቹ ላይ ጉዳት ለማድረስና ጫና ለመፍጠር ነው ሲሉ ጠበቆች አከለዋል፡፡

ዐቃቤ ህግ ባቀረበው የክሥ ቻርጅ ላይ ከአሸባሪ ጋር በመገናኘት፣ ድጋፍ በመስጠት፣ ሀገር በመክዳት፣ በመሰለል የሚሉ ቃሎች አሉ ያሉት የተከላካይ ጠበቆች ነገር ግን ወንጀሉ የተፈጸመበትን ጊዜና ቦታ አላስቀመጠም በማለት ሰፊ ህጋዊ ማብራሪያ አቅርበዋል፡፡

በመጨረሻ ፍርድ ቤቱ የዐቃቤ ህግን ክስና የተከላካይ ጠበቆችን መቃወሚያ ካደመጠ በኋላ በክሥ ቻርጁ ላይ ብይን ለመስጠት ለዛሬ ሃሙስ ህዳር 14 ቀን 2004 ዓ.ም ጊዜ ቀጠሮ ሰጥቶ የነበረ ሲሆን በቀጠሮው መሠረተ በዛሬው ዕለት ጉዳዩ በድጋሜ ታይቶአል።

በዚሁ መሠረት በዛሬው ህዳር 14 ቀን 2004 ዓም ከቀኑ በ9 ሰአት በዋለው ችሎት ላይ ሁሉም እስረኞች እጆቻቸው በካቴና ታስሮ ፍርድ ቤቱ ፊት መቅረባቸው ተዘግባአል።

በዛሬው ዕለት ተካሂዶ የዋለውን የፍርድ ቤት ድራማ ለመታዘብ በመቶዎች የሚቆጠሩ የእስረኞች ቤተሰቦች፤ የትግል አጋሮችና አድናቂዎች የተገኙ ቢሆንም ፖሊሶች ግን 20 ሰዎችን ብቻ እንደሚያስገቡ በመግለጣቸው አብዛኛው ህዝብ ሁኔታውን በውጭ ሆኖ ለመከታተል ተገዶአል።

ከመለስ ዜናዊ የተሰጠውን ብይን አስቀድሞ የተገነዘበውና ሂደቱን ህጋዊ ለማስመሰል ብቻ ደፋ ቀና እያለ ያለው የይስሙላው ፍርድ ቤት በዛሬው ውሎው ከአንደኛውና ከአራተኛው ክሶች በስተቀር ሌሎች ክሶች መሰረተ ቢስ ናቸው፣ አንደኛውና አራተኛውም ክሶች ቢሆኑ መሻሻል የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ አቃቢ ህግ ክሱን አሻሽሎ ለህዳር 20 ቀን ይዞ እንዲቀርብ በማለት ወስኖ እንዳሰናበታቸው ለማወቅ ተችሎአል። በተራ ቁጥር አንድ እና አራት ላይ የሰፈሩት ወንጀሎች ሽብር ለመፈጸም ማቀድና ከኤርትራ መንግስት ጋር አብሮ መስራት የሚሉት ናቸው።

የፖለቲካ እስረኞቹን ክስ ለመከታተል ከተለያዩ ኢምባሲዎች የመጡ ዲፕሎማቶችና የውጭ ጋዜጠኞች በብዛት በቦታው መገኘታቸውንም ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

መለስ ዜናዊ አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን በእጃችን ሳንይዝ አንድም ሰው አላሰርንም በማለት እንደአሻንጉሊት ለሚመለከታቸው ፓርላማ ተብዬ ስብስብ በቅርቡ ተናግሮ እንደነበር ቢታውስም እስካሁን በታዬው የፍርድ ቤት ሄደት ይህ ነው ሊባል የሚችል ተጨባጭነት ያለው አንድም ማስረጃ ለማቅረብ አለመቻሉ ድህረ ምርጫ 97 ከታየው የፖለቲካ ክስ የባሰ የሚያሳፍር ድራማ እየተሰራ መሆኑን የራሱ ካድሬዎች እየተናገሩ ነው።

## በአርበኛው የኔሰው ገብሬ ላይ የተከፈተው የስም ማጥፋት ዘመቻ

. . . (ከገፅ 2 የዞረ)

ከተፈታና ህይወቱም ካለፈ በሳምንቱ የአይምሮ በሽተኛ ነው መባሉ በጣም የሚያሳዝን ነው። የአይምሮ በሽተኛና እብድ ነበር በማለት ስም ማበላሸት በየኔሰው የተጀመረ አይደለም፣ ከአሁን ቀደም አንድ አቶ አበራ የሚባሉ የአካባቢው ነዋሪ የግብርና ባለሙያ እብድ ነህ የአይምሮ በሽተኛ ነህ ተብለው ከስራ ከተወገዱ ቦኋላ የህክምና ዶክተሮች ጤነኛ መሆናቸውን በማረጋገጣቸው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ተደርጉአል፣ በዚያ አካባቢ፣ እንዲህ አይነት ስም መስጠት አዲስ አይደለም፣ ለምን እንዲህ እንደሚደረግም ፈጽሞ አይገባኝም ብለዋል።

አቶ የእኔ ሰውን እብድ ነበር አሉ የተባሉት እህቱ ናቸው ነው የተባለው እንዴት ይመለከቱታል፣ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ አቶ ፍስሃ ሲመልሱ የሰው ልጅ አእምሮ ነጻነት ካጣ ለወንጀል ተባባሪና መሳሪያ መሆኑ የሚገርም አይደለም። ዋናው ጥያቄ እኒዚህ ሰዎች የአይምሮ ነጻነት አላቸው ወይ የሚለው ነው? በአካባቢው ከፍተኛ የነጻነት እጦት አለ፣ እውነት የመናገር፣ ያሰቡትንና የሚያውቁትን መግለጽ እጅግ ጠቃሚና ጥሩ ነበር። ነገር ግን የአካባቢው ሰዎች ይህን ማድረግ አይቺሉም። አንድ እህት እንደ ኢትዮጵያዊ ባህላችን ወንድሟ ከሞተ ቦኋላ እብድ ነበር ብላ ለህዝብ የምትናገርበት ሁኔታ በፍጹም ሲሆን የማይችልና የማይዋጥልኝ ነው። ነገር ግን ለመኖር ብለው ያሉት ሲሆን ይቺላል። ምናልባት የሚገርመው የየኔሰው እህትም ሆነች ሌሎች ዘመዶች ወይኔ አድርጉ ያላቸውን ባያደርጉ ነበር፣ እናም እኔን የወያኔ ባለስልጣኖች እያደረጉ ያለውም ነገር ሆነ የየኔሰው ዘመዶች አሉ የተባለው ነገር አዲስ አይደለም አያስገርመኝም፣ ብለዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org